


# የለቡ-ጀሞ
# ጊዜያዊ የብስክሌት መጋለቢያ መንገድ

## ደህንነቱ የተጠበቀ የብስክሌት ትራንስፖርት ፕሮግራም፣ አዲስ አበባ

Bloomberg Philanthropies
Bloomberg Philanthropies INITIATIVE FOR GLOBAL ROAD SAFETY
NACTO
Global Designing Cities Initiative
TUMI Transformative Urban Mobility Initiative
giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH
WORLD RESOURCES INSTITUTE

### የፕሮጀክቱ አጭር መግለጫ

# የለቡ-ጀሞ የብስክሌት መጋለቢያ መንገድ

**በአዲስ አበባ ሞተር አልባ ትራንስፖርት ስትራቴጂ ስር ከተማዋ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በደህንነቱ የተጠበቀ የብስክሌት ትራንስፖርት ፕሮግራም የ100 ኪ.ሜ የብስክሌት መንገዶች ለመገንባት እቅድ ይዛለች። የሶስት ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የለቡ-ጀሞ የብስክሌት መንገድ የዚህ ፕሮግራም የመጀመሪያ እርምጃ ማስተዋወቂያ ሆኗል።**



**በፊት**
መኪና-ያማከለ ንድፍ



**በኋላ**
ለሁሉም የሚሆን ቦታ

## የፕሮጀክቱ ግብ

የብስክሌት መንገዱ የተዘጋጀው በአዲስ አበባ ውስጥ የበለጠ ዘላቂነት ባላቸው አስተማማኝ የትራንስፖርት ዘዴዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ የተጀመረው ፕሮጀክት ሰርቶ ማሳያ በመሆን እንዲያገለግል ነው። ከተማዋ ለሁሉም ነዋሪዎቿ ሁሉን አቀፍ የሆነ የእንቅስቃሴ አማራጮችን የማቅረብ አጋጣሚዋ የሰፋ እንደመሆኑ የለቡ-ጀሞ ጎዳና ይህ የሚቻል መሆኑን ለማሳየት ታስቦ ዲዛይን የተደረገ ነው። መንገዱ የሚገኝበት ቦታ ከዚህ ቀደም በከተማዋ ከተደረጉ ሙከራዎች ልምድ በመቅሰም በርካታ የጉዞ መነሻዎችን እና መድረሻዎችን ያገናኛል፡ ፡ የዚህ ቦታ መረጣ ሂደት የጥናትን እና በብስክሌት አውታረ-መረብ ትስስር ውስጥ የወደፊት የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት እንቅስቃሴዎችን በጥንቃቄ የመምረጥ አስፈላጊነት አረጋግጧል። እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ አውታረ-መረቦችን መገንባት በዚህ የጊዜያዊ ሙከራ ወቅት ከነበረው እጅግ በላቀ ሁኔታ የብስክሌት ጋላቢዎች ቁጥር ከፍ የማድረግ አቅም አለው። ይህ ዲዛይን በአዲስ አበባ ውስጥ ጠንካራ የብስክሌት መጋለብ ባህልን ለማስፋፋት እገዛ ያበረከተ ሲሆን እርስ በርስ ከተያያዙ አውታረ-መረቦች ጋር እጅግ ሰፊ የሆነ አስተማማኝ ተጽእኖ ይኖረዋል።

## ጥቅም ላይ የዋሉ የዲዛይን ስትራቴጂዎች

በሁለቱም አቅጣጫ የነበረው ባለ ሶስት መስመር መንገድ በመታጠፊያው መስመር በሁለቱም በኩል ብስክሌቶች እንዲያሳልፍ የሚያደርግ የመንገዱን ጠርዝ ይዞ እንዲገነባ ተደርጎና በመንገድ ላይ የሚቆሙ መኪኖች በተቃራኒ አቅጣጫ የመንገዱን ጠርዝ ላይ እንዲቆሙ ሆነው እንደገና ተቀይሰዋል። በዚህ መንገድ ላይ የነበሩት ሰፋፊ የተሽከርካሪ መስመሮች ለብስክሌት መጋለቢያ የተመደቡ መንገዶችን ለማዘጋጀት በሚያመች መልክ ሰፊ የሆነ ቦታ የማግኘት እድልን ፈጥረዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ እና በትራፊክ አስተዳደር ኤጀንሲ የተመራው የማሻሻያ ስራ በአራት ቀናትና ሌሊት ፕሮጀክቱን በመተግበር መጨረስ ችለዋል ። በመንገዱ ርዝመት ልክ ከፕላስቲክ የተሰሩ ማካፈያዎች ከመንገዱ መለያ ቀቦች ጋር አብረው የተሰሩ ሲሆን በየመገናኛ ቦታዎች መታጠፊያዎችና የመጠላለፍ አደጋ ሊኖርባቸው የሚችልባቸው ቦታዎች ላይ አረንጓዴ የመለያ ምልክቶች ተቀምጠዋል። መታጠፊያዎች ላይ ለመንገድ ተጠቃሚዎች በመንገዳቸው ላይ ስለተሰራው አዲስ መሰረተ ልማት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ምልክቶች እና የመንገድ ቅብ ተድርጓል።




*ትራንስፖርት ቢሮ በተከታታይ በተከናወኑ የመስክ ላይ መረጃ መሰረት በማድረግ  የተጠናቀረ ነው።



**95%** የሚሆኑት የብስክሌት መንገዱ **ቋሚ** እንዲሆን ይፈልጋሉ።




**96%** የሚሆኑት ብስክሌት ጋላቢዎች በጊዜያዊው መሰረተ ልማት ላይ ብስክሌት ሲጋልቡ **በተወሰነ ደረጃ ደኅንነት** ተሰምቷቸዋል።



**65%** የሚሆኑ ደኅንነት የሚሰማቸው **ከትራፊክ ፍሰቱ የሚለያቸው** በመሰረተ ልማቱ የሚታዩ መለያዎች መኖራቸው መሆኑን ገልጸዋል።

# ወደ ስኬት የሚያመራ ጎዳናን መገንባት


እ.ኤ.አ በጥር 2020 ቀደም ሲል የነበረውን የመንገድ ጥግ የመቀየር ስራ ከመጀመሩ በፊት ሰፋ ያለ የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ተከናውኗል። ከትግበራ በኋላም በአራት ዙር እና በሶስት የተመረጡ የቀኑ ሰዓታት በመንገዱ ላይ በአጠቃላይ የብስክሌቶች እና የተሽከርካሪዎች ፍሰት ምን እንደሚመስል መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተካሂዷል። በእነዚህ አራት ዙሮች የተሰበሰበው መረጃ በአማካይ በሚከተለው ቻርት ላይ ተጠናቅሯል። በቁጥር ከተሰበሰበው መረጃ በተጨማሪ የሰዎችን ምላሽ ለመገምገም በመንገዱ በየእለቱ ከሚገለገሉ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ተጠቃሚዎች የጽሑፍ አስተያየት እና የቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል። የሚቀጥለው ቁጥራዊ አኃዝ የቀረበው ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የተገኙት መረጃዎች በማጠናቀር ነው።




ባለ ሁለት አቅጣጫ ጊዜያዊ የብስክሌት መጋለቢያ መሰረተ ልማት በመንገዱ ላይ ከተገነባ ወዲህ የብስክሌት ጋላቢዎች ቁጥር ጨምሯል።



**7.5** ጊዜ ያህል የብስክሌት ጋላቢዎች ቁጥር **ጨምሯል**




ለብስክሌት መንገድ ቦታ ተወስዶ የተደለደለ ቢሆንም በመንገዱ ላይ ያለው **የተሽከርካሪዎች ትራፊክ ፍሰት በነበረበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡** ፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች የመኪና መሄጃ መንገድ ስፋት በመቀነሱ የመንገዱን የማስተናገድ ችሎታ የጨመረው ሲሆን ይህ ጥረት የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ የሚያሻሽል መሆኑንም አሳይቷል።

# 3 ኪ ሜ ባለ ሁለት አቅጣጫ የብስክሌት መንገዶች

ቀለም ከተቀቡ እና ከተቀመጡ መለያዎች ጋር










# ነባራዊ ሁኔታዎች፣ የተወሰዱ ትምህርቶች እና መልካም አጋጣሚዎች ሲገመገሙ






## የመኪና ማቆሚያ

የሶስት ኪ.ሜ ርዝመት ባለው አዋሳኝ መንገድ መጠቀምን ጨምሮ በአካባቢው ላይ የተደረገ ጥናት በሁሉም የመንገዱ ክፍሎች እንዲሁም በመንገድ ዳር ላይ ባሉት በርካታ ህንጻዎች የግቢ ውስጥ ማቆሚያዎችን ጨምሮ በቂ የሆነ የመኪና ማቆሚያ አማራጮች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል። የብስክሌት መጋለቢያው መንገድ ዲዛይን ወደ ህንጻዎች የሚገቡም ሆነ የሚወጡ መኪኖች እንዲሁም የመንገድ ቅያሶች ምንም ችግር እንዳይደርስባቸው ተደርጎ የተሰራ ነው። በተጨማሪም በለቡ-ጀሞ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግቢ ውስጥ ሰፊ የመኪና ማቆሚያ ቦታ አለ። የመኪና ማቆሚያ ቦታ ቅነሳው ስር ነቀል ስላልሆነ የተደረገው የተሽከርካሪ አጠቃቀም አንፃር በዚህ አካባቢ ያሉ ነዎሪዎች የእንቅስቃሴ ምርጫዎቻቸውን ለመቀየር እንዲችሉ አጋጣሚዎችን ያመቻቸ ነው።

## የትራፊክ አስተዳደር

ከለውጡ "በፊት" እና ከለውጡ "በኋላ" የተሰበሰበው መረጃ እንዳመላከተው በትራፊክ ፍሰቱ ላይ ከፍተኛ የሚባል ተጽእኖ አልተፈጠረም። ምንም እንኳን ከመኪና መንገዶች ላይ ቦታ ቢወሰድም የመንገዱ መጥበብ የትራፊክ ፍሰቱን እንዳላስተጓጎለው እንዲያውም የተስተካከለ እንዲሆን አስተዋጽኦ ሳያበረክት እንዳልቀረ መረጃው ያሳያል፡ ፡ በአብዛኞቹ ቦታዎች የተፈጠሩ ማነቆዎች ምክንያቶች ህገወጥ በሆነ መንገድ መኪና አቁመው በሚሄዱ ሰዎች እና ደርበው በሚያቆሙ ሰዎች መሆኑ የተመዘገበ ሲሆን ይህ የደንብ ማስከበር ስራዎችን በመስራት እና በቦታው ላይ በግልጽ የሚታዩ ተጨማሪ ምልክቶችን በማስቀመጥ ሊቀረፍ የሚችል ነው።





## ሕግ ማስከበር

ከከተማዋ ኤጀንሲዎች ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በብስክሌት መንገዶች ላይ ሕገወጥ በሆነ መንገድ አብዛኛውን ጊዜ ለረጅም ሰዓታት የሚቆሙ መኪኖችን ለመከልከል በቂና ቀጣይነት ያለው አስገዳጅ ህግ በሥራ ላይ አልዋለም።

የትራፊክ ፖሊስ እና የደንብ አስከባሪ አካላት በብስክሌት መንገዱ ሁሉም ክፍሎች ላይ የሚቆሙትን መኪኖች ለመቆጣጠር ደንብ አስከባሪ ባለሙያዎችን በማሰልጠንና የተጠናከረ ጥረት በማድረግ በመመደብ ላይ ይገኛሉ።

## የመተላለፊያ መንገዶች አስተዳደር

በብስክሌት መንገዱ ላይ ያሉትን የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም ከግምት በማስገባት እና በለቡ-ጀሞ ያለውን የአኗኗር ሁኔታ የቃኙ የቀድሞ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ  የብስክሌት መንገዱ ንድፍ የተሰራው የተለያዩ የመንገድ ዳር እንቅስቃሴ አስፈላጊነትን ባገናዘበ መልኩ ነው፡ ፡ ከላይ በስዕሉ ላይ እንደሚታየው በአረንጓዴ የተሰመሩ ቦታዎች በዚህ መልኩ የተቀቡት ተሽከርካሪዎች ማቋረጥ የሚችሉባቸውን ቦታዎችን ለማሳየት ነው። እነዚህ ቦታዎች እቃ ጫኝ መኪኖች እና የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የብስክሌት መንገዱን አቋርጠው ወደ ህንጻ እንዲገቡ የሚፈቀድባቸው ቦታዎች ናቸው። የህግ አስከባሪ አካላት በመንገዱ ላይ የተገነቡት እነዚህ ቦታዎች በሁሉም ተጠቃሚዎች ዘንድ ጥንቃቄ በታከለበት ሁኔታ በጥቅም ላይ እየዋሉ መሆኑን ቅድሚያ ሰጥተው የመከታተል ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው።



## መከላከያ/መለያ

ፕሮጀክቱ በመጀመሪያ ተግባራዊ የተደረገው 1400 በሆኑ ጎልተው በሚታዩ ለረዥም ጊዜ ሊያገለግሉ የሚችሉ ተንቀሳቃሽ መለያዎችን በመጠቀም ነበር። ከጊዜ በኋላ በተለይም በመኪና መታጠፊያ ቦታዎች ላይ ተተክለው የነበሩት መለያዎች በመኪኖች በመመታት ከፍተኛ አደጋ ሊደርስባቸው ችሏል። ተጋላጭነት በተሻለ ሁኔታ በሚጠብቅ ሁኔታ ከጠንካራ ኮንክሪት በተሰሩ መለያዎች ተተክተዋል። ጎልተው እንዲታዩ የሚያደርግ ቀለም ተቀብተውዋል።



## ብስክሌት የመጋለብ ባህል

ከተማዋ ምቹ የብስክሌት መጋለብ ፕሮግራም በጀመረችበት ጊዜ የነበረው የብስክሌት መጋለብ ባህል አነስተኛ የነበረ ቢሆንም እንኳን ከዚህ ፕሮጀክት የተሰበሰበው መረጃ በመንገዱ ላይ የእለታዊ ብስክሌት ተጠቃሚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑን አሳይቷል። ልጆችና ቤተሰቦቻቸው የብስክሌት መጋለብ ባህል እንዲያዳብሩ በአቅራቢያው በሚገኙ የህብረተሰብ ማዕከላትና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የስልጠና ሜዳዎች እየተዘጋጁ ነው። ይህን መንገድ ከሌሎች አውታረ መረቦች በተለይም ብስክሌት በቀላሉ ሊገኝባቸው የሚቻልባቸው መንገዶች ላይ መዋዕለ ንዋይ ከሚያፈሱ እንቅስቃሴዎች እና ደህንነቱ የተጠበቀ ብስክሌት ስለመጋለብ ግንዛቤ ከሚሰጡ ትምህርቶች ጋር ማቀናጀት አስፈላጊ ነው።



## ዝቅተኛ የብስክሌት ባለቤትነት መጠን

ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ  ምክኛት በአዲስ አበባ ያለው የብስክሌት ተጠቃሚ ብዛት ዝቅተኛ ነው።  ባለፉት ዓመታት ጎረቤት ከተሞች ከፍተኛ ብስክሌት መጋለብ ባህል እድገት ቢያሳዩም  በአዲስ አበባ ያለው የብስክሌት ባለቤትነት አነስተኛ ነው።  በአገር ውስጥ የብስክሌት አምራች አለመኖርና ከውጭ የሚመጡ ብስክሌቶች ከፍተኛ ቀረጥ የሚጣልባቸው መሆኑ የከተማዋ ሰፊ ሕዝብ ብስክሌቶችን የመግዛት አቅም እንዳይኖረው አድርጓል። ብስክሌት መጋለብ እንዲስፋፋ ብሎም ይህ የአካል እንቅስቃሴን የሚያጎለብት ርካሽ የእንቅስቃሴ አማራጭ ለሁሉም ተደራሽ ይሆን ዘንድ ቀረጥ እንዲቀንስና ዘርፉ ድጋፍ እንዲያገኝ ጥረቶች መደረግ ይኖርባቸዋል።




## የብስክሌት ትራንስፖርት አውታረ-መረብ ዝርጋታ አስፈላጊነት

በለቡ-ጀሞ መንገድ ላይ የብስክሌት ጋላቢዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ በሌሎች መዳረሻዎችና አጎራባች መኖሪያ መንደሮች ላይ ተመሳሳይ መንገድ እንዲኖር ፍላጎቱ እየጨመረ ይሄዳል። በተመሳሳይ ጊዜ የተፈጠረውን መነቃቃት በመጠቀም በሌሎችም የከተማዋ ክፍሎች ተመሳሳይ ግንባታዎችን ለማካሄድ የሚያስችሉ አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ። በከተማይቱ የተለያዩ ቦታዎች በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ የሚደረጉት የልማት ተግባራት የተለያዩ የንድፍ ስትራቴጂዎችን በመጠቀም እና የእያንዳንዱን አካባቢ ልዩ ፍላጎት ከግምት ባስገባ መልክ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የብስክሌት መጋለቢያ አውታረ-መረቦችን ለማስፋፋት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።





## የለቡ-ጀሞ ጊዜያዊ መንገድ በቁጥር ሲገለጽ

**ለማስፈጸም የወሰደው ጊዜ**




**96 ሰዓታት**
**(የዲዛይን ጊዜን ሳይጨምር)**


**በስራው ላይ የተሳተፉ ሰዎች ቁጥር**



**ከ100 በላይ**



**1400 መለያ**
ብስክሌት ጋላቢዎችን
ከተሽከርካሪዎች ለመለየት



**10,000ካሬ ሜትር**
ቦታ ለብስክሌት ጋላቢዎች
እንደገና ተለይቷል

Bloomberg Philanthropies

Bloomberg Philanthropies
INITIATIVE FOR GLOBAL ROAD SAFETY

NACTO

Global Designing Cities Initiative

TUMI
Transformative Urban Mobility Initiative

giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH

WORLD RESOURCES INSTITUTE